የሰ/መ/ቁ. 41608

ሐምሌ 22 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካቾች፡-** እነ ሙላቱ አንበርብር - ቀርቧል

**ተጠሪ፡-** ወ/ት ታመነች ዮሴፍ መና ወኪል - ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ የቀበሌ 06 አስተደደር ማሕበራዊ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች የስር ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ ነበሩ አመልካቾች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ በተጠሪ የመኖሪያ ቤት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የሆኑ ግለሰቦች ከፍተኛ የድምጽ ማጉያ በመጠቀም በሚያካሂዱት ጩኸት አካባቢውን በማወካቸው በመኖሪያችን ልናርፍ አልቻልንም በሚፈጠረው የድምጽ ብክለት በጤናችን ላይ ጉዳት እያደረሰበን ስለሆነ የድምጽ ብክለቱ ይወገድልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ ይህ የሐይማኖት ጥላቻ በመሆኑ በአድማ የቀረበ ክስ ነው፡፡ የማንንም መብት ሣንጋፋ መንግስት ለሐይማኖትና ለእምነት ነፃነት የሰጠው ሕገመንገስታዊ መብት እንዲከበርልን ተደርጐ የማምለክ መብታችን ተጠብቆ እያለ ድንጋይ እየተወረወረብን በደል እየደረሰብን ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የማህበራዊ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ በመመርመር አመልካቾች ያቀረቡትን አቤቱታ አስመልክቶ ሁከት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ሲል የመሰረት ልማት ቴክኒሻን(ባለሙያ) ወደ ስፍራው በመላክ ሁከት እንዳለ በማረጋገጥ ተጠሪዎች በሌላው ሰው ላይ ሁከት እየፈጠሩ ህገ-መንግስታዊ መብታችን እየተጠቀምን ነው ማለቱ ሕጉን በተሣሣተ መተርጐም ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህ በአዋጅ ቁ. 12/96 አንቀጽ 5/3/ መሰረት፣በወንጀል ሕግ 815/1/ የሌሎችን ስራና ሰላም ማወክ ሆኖ ስላገኘው ተጠሪዎች 100 ብር (መቶ ብር) ይቀጡ መኖሪያ ቤቱ ለተፈቀደለት አላማ ብቻ ይዋል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለአ/አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ጉዳዩ የቀረበለትም ፍ/ቤት የግራ ቀኙን በማከራከር በጭብጥነት የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ መወሰን ስልጣን አለው ወይ? የሚለውን በማየት ሲወስን የክልል 14 መስተዳደር ደንብ ቁጥር 1/1986 አንቀጽ 10/2/ በመጥቀስ ይህን ደንብ የጣሰ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የመንግስት አካል ተገቢውን አስተደደራዊ ውሣኔ እንደሚወሰድበት ከተጠቃሹ ደንብ አንቀጽ 17/1/ሀ/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ ተጠቃሹን ደንብ የጣሰ በቅድሚያ አስተዳደራዊ ውሣኔ እንዲሰጥበት ማድረግ እንጂ በቀጥታ ክስ በፍ/ቤት ክስ የማይመሰረትበት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይም አመልካቾች ይህን ለማድረጋቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም በአስተዳደር አካል ውሣኔ ካልተሰጠ ደግሞ የስር ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን የለውም በመሆኑም የስር ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ በማለት ሲወስን የአሁን አመልካቾችም በዚሁ ውሳኔ ባለመስማማት ለአ/አበባ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ጉዳዩ የቀረበለትም ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሣይሰማ አመልካቾች

በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የፍ/ብሔር ክርክር በመሆኑ በስር ፍ/ቤት በተወሰነው መሰረት በቅድሚያ የሚመለከተው አስተዳደራዊ አካል ውሳኔ መስጠት ይገባል መባሉ በአግባቡ ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች ህዳር 24 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በአ/አ/ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና በከተማው የከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረምልን ይገባል በማለት አመልክቷል፡፡

በዚህም መሰረት የተጠሪን እና የአመልካችን የቃል ክርክር በችሎት ሰምተናቸዋል፡፡፡ ጉዳዩ በሰበር እንዲታይ የቀረበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ መስተናገድ ያለበት በአ/አ/አስተዳደር አዋጅ ቁ. 12/96 አንቀጽ 5/3/ አንፃር ሣይሆን በአስተዳደር ደንብ ቁጥር 1/86 አንቀጽ 10/2/ እና 17/1/ሀ ነው በማለት የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የማህበራዊ ፍ/ቤትን የመሻራቸውን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ የግራ ቀኙ ካሰሙት ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር ማገናዘብ መርምረናል፡፡

በመሆኑም የጉዳዩን አመጣጥ ጠቅለል ባለ መልኩ ስናይ የአሁን አመልካቾች በስር ክሣቸው የፕሮቴስታንት ተከታዮች በተጠሪ መኖሪያ ቤት ከፍተኛ የድምጽ ማጉያ በመጠቀም በሚያካሄዱት ጩኸት አካባቢውን በማወክ በድምጽ ብክለት በጤናችን ላይ ጉዳት እያደረሱብን ነው፡፡ ይህ ድምጽ ይወገድልን በማለታቸው ምክንያት፡፡ የማህበራዊ ፍ/ቤቱም እንደተባለው የድምጽ ብክለት አለ በማለት ተጠሪ (100) ብር (መቶ ብር) እንዲቀጡ ሲወስን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን በማከራከር ጉዳዩ በፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት በመስተዳደር አካል መታየት ነበረበት ስለዚህ የዳኝነት ስልጣን የለህም በማለት የማህበራዊ ፍ/ቤትን ውሳኔ ሲሽር የከተማው የከፍተኛው ፍ/ቤትም በተመሣሣይ ምክንያት የከተማውን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት አጽንቷል፡፡

እንግዲህ በዚህ ጉዳይ በዋናነት ሊታይ የሚገባው የስር ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለው ሆኖ አግኝተነዋል በመጀመሪያ ደረጃ የቀበሌ የማህበራዊ ፍ/ቤቱ አዋጅ ቁ. 12/96 በአዋጅ ቁ. 31/99 መሻሻሉን ከግንዛቤ ሣያስገባ እና ይህ አዋጅ ቁጥር 31/99 ስልጣን ባልሰጠው ሁኔታ ውሣኔ ሰጥቷል የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ይህን በጥልቀት ሣያጤነው ምንም እንኳ የስር ፍ/ቤት ስልጣን የለውም ቢልም ምክንያት ያደረገው የግራ ቀኙ ክርክር መጀመሪያ በአስተዳደራዊ አካል መታየት ነበረበት በሚል ነው፡፡ የከፍተኛውም ፍ/ቤት ይህንኑ አጽንቷል፡፡ በመሰረቱ ለክርክሩ መንስኤ አመልካቾች በተጠሪ ድርጊት የጽምጽ ብክለት ጉዳት አድርሶብናል የሚል ሲሆን ጉዳዩም የፍትሐብሔር ክርክር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ሊስተናገድ የሚገባውም በፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 1225 መሰረት ነው፡፡ ይህንንም ጉዳይ ለማየት ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደራዊ አካል እና የአ/አ ከተማ ፍ/ቤቶች ስልጣን አይደለም፡፡

በመሆኑም ይህ ታልፎ በስር ፍ/ቤቶች መታየቱ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአስተዳደሩ ማህበራዊ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0207 በቀን 2/5/2000 የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 877/00 በቀን 01/9/2000 እና የከተማው ይግባኝ ሰሚ በመ/ቁ. 08015 ቀን 12/2/2001 የተሰጡት ውሣኔዎች ተሽሯል፡፡
2. የማህበራዊ ፍ/ቤትም ሆነ ከአ/አ/ከተማ ፍ/ቤቶች ስልጣን የላቸውም፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

# ባንክና ኢንሹራንስ